# ው ይ ይ ት

## ከግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

### ክፍል ኣንድ

# መ ግ ቢ ያ

(በ-ኣብርሃም ያየህ)

መስከረም 24 ቀን 2006 ዓ.ም. (October 4, 2013)

ማስታወሻ፤ በዚህ "መግቢያ" ፅሑፌና በቀጣዮቹ ተከታታይ ፅሑፎቼ፥ ገዢውን ፓርቲ የምጠቅሰው በኣህፅሮት "ወያነ" በማለት ይሆናል። ኣንዳንዶቹ እንደሚያስቡት "ወያነ" የሚለው ኣጠራር "ህወሓት"ን ብቻ የሚገልፅ እንደሆነና፥ ኣሁን ኢትዮጵያን እየገዛ ያለው ስርዓት መጠሪያው "ኢህኣዴግ" ነው በማለት ሲናገሩ ይደመጣሉ። ይህ ካለማወቅ የመነጨ ኣባባል ነው። "ኢህኣዴግ" የገዢው ቡድን ያማርኛ ቋንቋ መጠሪያው ሲሆን፥ ቡድኑ ራሱን በትግርኛ ቋንቋ የሚጠራው ደግሞ "ናይ ኢትዮጵያ ህዝቢታት ወያናይ ዴሞክራሲያዊ ግምባር" (ኢህወዴግ) በማለት ነው። "ወያናይ" የሚለው ቅፅል-ስም "ወያነ" ከሚለው ስም የፈለቀ ሆኖ "ኣብዮታዊ" የሚለውን ያማርኛ ቃል እንዲወክል በራሱ በገዢው ቡድን የተመረጠ ስያሜ ነው። ስለሆነም፥ በተለየ ምክንያት "ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ"ን ኣስመልክቼ ስጠቅስ "ህወሓት" በሚል ሲሆን፥ ገዢውን ቡድን "ኢህኣዴግ/ኢህወዴግ"ን ስጠቅስ ግን "ወያነ" በሚል ይሆናል።

ይህ የሌሎች ቀጣይ ፅሑፎቼ መግቢያ፥ የግንቦት ሰባት ዋና ፀሓፊ ኣቶ አንዳርጋቸው ፅጌ በያዝነው ኣዲስ ዓመት ዋዜማ ከኢሳት ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ[1] ላይ ተመርኩዤ በሚቀጥሉት ሳምንታት በተለያዩ ርእሶች በተከታታይ ለማቀርባቸው መጣጥፎቼ ጠቃሚ መንደርደሪያ ነው። መጣጥፉ በተለይ የሚያተኩረው ከሃያ ዓመት በፊት የኤርትራን ነፃነት ኣስገኘ በተባለለት ህጋዊ ያልሆነ ሬፈረንደም ላይ ነው። ይህ ኣስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት፥ ከኤርትራ መንግስትና ህዝብ ለሚደረግ ማንኛወም ግኑኝነት የሪፈረንደሙ ኣፈፃፀምና የወያኔ ስርዓት ለኤርትራ ነፃነት የቸረው እውቅና ህጋዊ ያለመሆኑን ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ህዝብ  ኣስቀድሞ ማሳየት ኣስፈላጊ በመሆኑ ነው። ስለሆነም፥ ለወያኔ መሪዎች የረጅም ጊዜ ድብቅ ዓላማ ማሳኪያ ተብሎ፥ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጀርባ በወያነ መሪዎች የተስተናገደው የኤርትራ ሬፈረንደም ኣፈፃፀም ህጋዊነት ያልተላበሰ መኖሩን በሰነድ ኣስደግፌ እገመግማለሁ። ስለዚህ፥ የሁሉም ቀጣይ ስራዎቼ መጋቢና የጀርባ ኣጥንት የሆነው ይህ መግቢያ መጣጥፌ እጅግ ወሳኝ የሆነ ጭብጥ ያዘለ ስለሆነ፥ ኣንባቢዎቼ በጥሞና እንዲመለከቱት በቅድሚያ ኣስታውሳለሁ።

የኤርትራ ነፃነት በተመለከተ የወያነ መሪዎችና ቲፎዞዎቻቸው[2] ሁሌም ሊያስረዱን የሚፈልጉት፥ ኤርትራ ነፃነቷን ያገኘችው በነሱ ፍላጎት ሳይሆን ሻዕቢያ ኢትዮጵያን በጦርነት ኣሸንፎ ኤርትራን ስለተቆጣጠረ ምንም ማድረግ የሚቻል ነገር ያለመኖሩን ነው። ይሁን እንጂ ይህ ትክክለኛ መግለጫ ኣይደለም።

በመጀመሪያ ደረጃ፥ ሻዕቢያ ያሸነፈው (ይህ ቀረው የማይባል የወያነ ድጋፍ ታክሎበት) ደርግን ነው እንጂ የኢትዮጵያን ህዝብ ኣይደለም። ሻዕቢያ የኢትዮጵያን ህዝብ ማሸነፍ እነደማይችል ደግሞ የባድመ ቁርቁስ በሚገባ ኣሳይቶን ኣልፏል። ቁርቁሱ ኣሳዛኝና ኣላስፈላጊ ባይሆንም። ከዚያ ባሻገር ደግሞ፥ የኤርትራም ይሁን የሌላ ኣገር ነፃነት በጡንቻ ሊረጋገጥ ኣይችልም። ምክንያቱም፥ በጡንቻ የተገኘ ነፃነት በጡንቻ ሊነጠቅ ይቻላልና። የወያነ ቁንጮዎች የኤርትራ ነፃነት በጡንቻ የተገኘ ነው የሚሉን ከሆነ፥ ዛሬ ኢትዮጵያ ከሻዕቢያ በበለጠ በኤኮኖሚዋና በመከላከያ ኃይሏ ጡንቻዋን ያፈረጠመች ኣገር ስለሆነች፥ የኤርትራን ነፃነት በኃይል መግፈፍ ትችላለች ብለን ልንደመድም እንችላለን ማለት ነው። ነፃነት በህግ ይረጋገጣል እንጂ በጉልበት ኣይገኝም። ሻዕቢያ የሬፈረንደም ሃሳብ ያቀረበውም የኤርትራን ነፃነት ህጋዊነት ለማልበስ ሲል ነው። በተቀረ፥ ኤርትራን በኃይል ተቆጣጥሬኣለሁና ደህና ሁኑ ብሎ በተሰናበተን ነበር።

የኤርትራ ነፃነት በህግ ተረጋግጦ በዓለም ህብረተሰብ እውቅና ሊያገኝ የሚችለው ደግሞ፥ የኢትዮጵያ ህዝብ በወከለው መንግስት ወይም ጉዳዩ በሬፈረንደም ኣማካኝነት ለኢትዮጵያ ህዝብ ቀርቦ፥ ህዝቡ በቃን ኤርትራ ትሂድ ብሎ ሲወስን ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ በቀጥታ በሬፈረንደም ወይም በወከለው ፓርላማና መንግስት ኣማካኝነት እውቅና ካልሰጠ የኤርትራ ነፃነት ብሎ ነገር

[1] የኣቶ ኣንዳርጋቸው ቃለ-መጠይቅ ያልተከታተሉ ሰዎች ይህንን የኢሳት ድረ-ገፅ (ሊንክ) በመጎብኘት ሊያዳምጡ ይችላሉ።
http://ethsat.com/video/esat-yesamintu-engida-ato-andargachew-tsege-sep-2013-ethiopia/

[2] የወያነ ደጋፊዎችን "ቲፎዞውች" የምልበት ምክንያት ለወያነ መሪዎች የሚሰጡት ድጋፍ ያንድ የእግር ኳስ ቡድን ኣባላት ወይም ደጋፊዎች ለቡድናቸው ከሚሰጡት ድጋፍ በማንኛውም መለኪያ የማይለይ በመሆኑ ነው። የኳስ ቡድን ደጋፊዎች ቡድናቸው ሲጠቃ/ሰበድል ሆነ ሲያጠቃ/ሲበደል የሚሰጡት ግብረ-መልስ ሁሌም መደገፍና እና መደገፍ ብቻ ነውና! ይሁን እንጂ፥ የህዝብንና የኣገርን ጉዳይ በተመለከተ የፖለቲካ መሪዎች ሲያጠፉም ጭምር የሚሰጠው ድጋፍ እንደኳስ ቡድን ድጋፍ የሚመስላቸው ካሉ፥ እነሱንም የጥፋቱ ተካፋይ መሆናቸውን ቆም ብለው ሊያስተውሉ ይገባቸዋል።

የለም። ከዚህ አካሄድ ውጭ፥ ነፃነት በጉልበት የማይገኝ መሆኑን ለማስረዳት ረጅም ርቀት መጓዝ ኣያስፈልገንም። በቀላል መንገድ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ሁሉም የሚያውቀቀውን ኣንድ ተጨባጭ ምሳሌ ልጥቀስ።

የቅርብ ጎረቤቶቻችን የሆኑት ሶማሊላንድና ፑንትላንድ በጡንቻዎቻቸው ከሶማሊያ ተለይተው (በኣንፃራዊ እይታ) ዴሞክራሲያዊ የሆነ ስርዓት መስረተው መኖር ከጀመሩ ዘመናት ኣስቆጥረዋል። ይሁን እንጂ፥ እንደ ወያነ ያለ እውቅና የሚሰጣቸው ሊጋሽ ስርዓት ሞቃዲሾ ላይ ባለመኖሩ፥ ባንዴራቸውን በዓለም መንግስታት ግቢ ለማውለብለብ ኣልቻሉም። ኣይችሉምም። ስለሆነም፥ እኛ ለወያነ መሪዎች እያልን ያለነው፥ ጦር ሰብቃችሁ ለምን ኤርትራን ኣላስቀራችሁልንም የሚል ኣይደለም። እኛ የምንለው ያለ፥ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ዘላቂ ጥቅምና ህልውና ግምት ውስጥ ባላስገባና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ሬፈረንደሙን ኣስፈፅማቿል፤ የህዝብ ውክልና ሳይኖራችሁ ለኤርትራ ነፃነት እውቅና መስጠታችሁ ተገቢ ኣይደለም፤ ይህንን በማድረጋችሁ ደግሞ በሃገር ክህደት ወንጀል ተከሳችሁ ለፍርድ ትቀርባላችሁ የሚል ነው።

ይህ ኣስደንጋጭ ክስ ነው። ስለሆነም፥ የእርቀሰላም መድረክ ይከፈትና የወያኔ መሪዎች በዚህ ጥፋታቸው ምክንያት ካለባቸው ጭንቀት የተነሳ ትግራይንም ገንጥለው የቀረችዋን ኢትዮጵያ እንዳይበታትኑብን መተንፈሻ እንስጣቸው እያልን ስንወተውት፥ እንደነ ስብሓት ነጋና በረከት ስምኦን ያሉ ኮሚኮች "የምን እርቀ ሰላም? የተጣላ ሰው የለም፥ ልዩነታችን የመስመር ልዩነት ነው፥" ወዘተ. እያሉ ይቀልዱብናል። ክሱ ግን የኔ ክስ ብቻ ኣይደለም። በተደራጁ ኃይሎች ጭምር፥ በምርጫ ማኒፌስቶ ተቀናብሮ፥ የኢትዮጵያ ህዝብ ድምፅ ሰጥቶበት፥ በምርጫ-97 ቅንጅትን አንፀባራቂ ድል ለማስመዝገብ ያስቻለው ክስ ነው። የቅንጅት ማኒፌስቶ ካረቀቁ ክቡራን መሃንዲሶች ዶ/ር. ብርሃኑ ነጋና ኣቶ ኣንዳርጋቸው ፅጌ ዋናዎቹ ስለሆኑ፥ ይህንን ማኒፌስቶ ያዘለውን ኣስደንጋጭ ክስ እዚሁ መጥቀስ ኣግባብ ያለው ይመስለኛል። 133 ገፆችን ያካተተው የነ ዶ/ር. ብርሃኑና ኣቶ ኣንዳርጋቸው ቅንጅት የምርጫ ማኒፌስቶ በገፅ 82 "የሃገር ሉዓላዊነት መደፈር" በሚል ርእስ ስር ያሰፈረውን እንመልከት። (እጠቅሳለሁ።)

> "የወያኔ/ኢህኣዴግ ኣገዛዝ የመንግስትን ስልጣን በጠመንጃ ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሃገሪቱን ሉኣላዊነትና የህዝቡን ብሄራዊ ጥቅሞች ለውጭ ኃይል ኣሳልፎ በመስጠት በሃገሪቱ ታሪክ ወስጥ ታይቶ የማይታወቅና ወደር የማይገኝለት የክህደት ተግባር ፈፅሟል። የኤርትራን ግንጠላ የሚደግፍ ህዝበ ውሳኔ [ሬፈረንደም] እንዲደረግ የፈቀደው <u>የኢትዮጵያን ጥቅም እንደሚጎዳ ኣስቀድሞ እያወቀና ሆን ብሎ ነው</u>። የሃገሪቱን ጥቅሞች የሚከላከል፥ የህዝቡን ሃሳብና ፍላጎት የሚወክል በህዝብ የተመረጠ ህጋዊና ቋሚ መንግስት በሌለበት የሽግግር ወቅት የሻዕቢያን ሃሳብ ደግፎ ለኤርትራ ግንጠላ የተባበሩት መንግስታትና የኣፍሪካ ኣንድነት ድርጅት እንዲተባበሩ ማመልከቻ የፃፈውና ኢትዮጵያ ወስጥ ድምፅ ለሚሰጡ ኤርትራዊያን ዳስና ድንኳን ከማዘጋጀት ጀምሮ ጠቅላላውን ሂደት ስፖንሰር በማድረግ የግንጠላው ተዋናይ ሆኖ የከረመው ይህንን እንዲፈፅም የሚያስችል ህጋዊ ውክልና ሳይኖረው ነው። <u>የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም የሚወክሉ ሃሳቦች በነፃነት እንዳይንሸራሸሩ መድረኩ ሁሉ በተዘጋበት ሆኔታ ከሻዕቢያ ጋር ተመሳጥሮ ከህዝቡ ፈቃድና እውቀት ውጭ ሂደቱ [የሬፈረንደሙ ሂደት] የሃገሪቱን ጥቅም በሚጎዳ መንገድ እንዲከናወን ኣደረገ</u>። ህዝበ ውሳኔው [ሬፈረንደሙ] ከመካሄዱ በፊት መፍትሄ ማግኘት የነበረባቸው የድንበር ጉዳይ፥ የባህር ቤት ባለቤትነት ጉዳይ፥ ኤርትራ ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ኤርትራዊያን ጉዳይ ምንም ዓይነት ትኩረት ኣላገኙም ነበር። <u>በጣም የሚገርመው የኤርትራ ወረራ ዋዜማ ኣካባቢ የድንበር ጉዳይ ኣጨቃጫቂ ሆኖ ሲወጣ ጉዳዩ የሃገር መሆኑ ቀርቶ ከሻዕቢያና ከህወሓት ኣመራሮች የተወከሉ ኣባላት የሚገኙበት የድንበር ኮሚሽን ኣቋቁመው በምስጢር የሚደራደሩበት ሆኔታ ተፈጥሮ ነበር"</u> (የጥቅሱ መጨረሻ፤ ኣፅንኦት/ሰረዝ የኔ።)

የምፅኣቱ እንቆቅልሽ፥ ይህንን ክስ ሲደረድሩ የነበሩና፥ ምስኪን የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ልጆች ትርጉም በሌለው ጦርነት ወስጥ ተማግደው እንዲተራረዱ ሲደረግ ከወያነ መሪዎች ጎን ተሰልፈው ድንጋይ ያቀበሉት የግንቦት ሰባት ቱጃሮች ዛሬ ኣቶ ኢሳያስን የክርስቶስ ታናሽ ወንድም ነው ብለው የሚያቆላምጡና የሚክቡ ሰዎች ሆነው መገኘታቸው ነው። (ይህ ከባድ ክስ፥ በምርጫ-97 ማግስት የወያነ መሪዎችን ብቻ ሳይሆን ሻዕቢያንም ያርበደበደ እንደነበረ በቀጣይ ፅሁፎቼ በተራ ቁጥር 7 እና 8 በዝርዝር እመለስበታለሁ።)[3]

"ኤርትራ ነፃነቷን የተቀዳጀችው በሻዕቢያ ጡንቻ ነው" የሚለው የወያኔ መሪዎች ጉንጭ ኣልፋ ኣሉባልታና የግንቦት ሰባቶች ትያትርዊ ተውኔት ወደጎን ትተን፥ ዛሬም፥ ሁልጊዜም፥ የኤርትራ ሬፈረንደም ኣፈፃጸም ጉዳይ የምናነሳው በወያነ መሪዎች መልካም ፈቃድና ፍላጎት የተቸረውና፥ በዓለም መንግስታት እውቅና የተሰጠውን የኤርትራ ነፃነት ለመቀናቀን ኣስበን ኣይደለም። የኤርትራን ሬፈረንደም እንደ ኣንድ ዋቢ ጉዳይ አድርገን የምናነሳበት ልዩ ምክንያት ኣለን። ባንድ በኩል የወያኔ መሪዎችን ማንነት ለህዝባችን የምናጋልጥበት ጉዳይ ስለሆነ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፥ የስጋ ዘመዳሞች የሆኑትና የጋራ ጂኦ-ፖለቲካዊና ስትራተጂካዊ ጥቅሞችና ችግሮች ያሏቸው የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች፥ ያለ ምንም ተጨማሪ ጦርነትና እልቂት፥ ሁሉንም በሚያረካ ሆናቴና፥ በሰላማዊ መንገድ ኣሁን ከገቡበት ኣዘቅት ማስውጣት ይቻላል ከሚል ፅኑ እምነት ተነስተን፥ ከዚሁ በተያያዘ ሬፈረንደሙ ህጋዊ ያለመኖሩን ለኤርትራ ህዝብ ጭምር ማስረዳት ለጉዳዩ ፋይዳ ያለው ግብኣት በመሆኑ ብቻ ነው።

[3] http://www.awrambatimes.com/wp-content/uploads/Dialogue_with_G7_Notice.pdf

ከዚህ በተጨማሪ፥ የወያነ ኣመራር፥ ያለ ህዝብ ውክልና ያስፈጸመው ሬፈረንደም የኢትዮጵያ ህዝብ እውቅና ስላልሰጠውና ስለማይሰጠው፥ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር፥ በረጅሙ የኤርትራን ህዝብ ኣደጋ ላይ የሚጥል ስለሆነም ጭምር ነው። ሻዕቢያም ይህንን በሚገባ የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ትርጉም በሌለው ጦርነት ገብተንና ከወያኔ መሪዎች ጎን ተሰልፈን የኤርትራን ህዝብ ከምንወጋ ሌላ ነገር እንዘይድ ብለን እኛ ከኤርትራ ጋር ውይይታችን የከፈትነውም ከዚሁ ጭብጥ ተነስተን ነው። (ይህንን በተመለከተ በሚቀጥለው ሳምንት በሚለቀቀውና "ከኤርትራ መንግስትና ህዝብ ጋር የሚደረግ ግኑኙነትና ትብብር ለምን?" በሚል ኣርእስት - በተራ ቁጥር 2 - በዝርዝር እመለስበታለሁ።)

ስለዚህ፥ ከኤርትራ መንግስትም ሆነ ህዝብ ማንኛውም ዓይነት ውይይት የሚደረግ ከሆነ፥ የውውይቱ መክፈቻና መንደርደሪያ ይህ ህጋዊ ያልሆነ የሬፈረንደም ኣፈፃጸምና፥ ህዝባዊ ውክልና ያልነበረው የወያኔ ስርዓት ለኤርትራ የሰጠው እውቅና መሰረት በማድረግ መሆን ይኖርበታል።

ይህ የሬፈረንደም ጉዳይ መነሳት ኣስፈላጊ ሆኖ ያገኘሁበት ተጨማሪ ምክንያት ደግሞ፥ ኣቶ አንዳርጋቸው ፅጌ፥ ከኢሳት ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ፥ ከኤርትራ ጋር የሚደረግ ግንኙነት በሻዕቢያ ድጋፍ የወያነን ስርዓት ለማስወገድ ይቻላል በሚል እሳቤ ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ነው። ይህ በስልትም በስትራተጂም የተሳሳተ ስሌት ነው። በበኩሌ ከሻዕቢያ በሚገኝ ድጋፍ የወያነ ስርዓት ይሽነፋል የሚል ህልምም፥ ኣስተሳሰብም፥ ስሌትም የለኝም፤ ኖሮኝም ኣያውቅም። ወደ ኤርትራ ስሄድም ሆነ፥ "የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፤ (ትህዴን)" ከሌሎች ጓዶች ጋር ሆነን ስንመሰረትም፥ የወያነን ስርዓት በሻዕቢያ ጠመንጃ መጣል እንችላለን ብለን ኣይደለም። የወያነን ስርዓት በቀላሉና ያለምንም ደም መፋሰስ ለማሰናበት የሚቻለው ከጠመንጃ ይልቅ ሌላ ህዝባችንና የመከላከያ ሰራዊታችንን በሚገባ የሚያሳምን ከጎናችን የሚያሰልፍ ነገር ከኤርትራ በኩል ማስገኘት ይቻላል ከሚል ስሌትና ጭብጥ በመነሳት ነው። (ትህዴን የመሰረትንበት ምክንያት በራሱ ሰፊ ታሪክ ያለው ስለሆነ በቀጣዩ ፅሁፎቼ በተራ ቁጥር 5 ይፋ የማደርገው ይሆናል።)[4]

ከዚህ በተረፈ፥ የወያነን ስርዓት በሻዕቢያ ጠመንጃ መጣል የሚቻል ቢሆን ኖሮ እንኳ፥ ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ተስማምተውበት፥ ኣምነውበትና ተካፍለውበት የሚደረግ እንጂ በግንቦት ሰባትና በትህዴን ሽርክና[5] ብቻ ሊከናወን ይቻላል ብሎ ማሰብ ኣይቻልም። እኔና መሰሎቼም "የሽማግሌዎች ምክር ቤት" ለመመስረት ያቀድነውና በዚያ ምክር ቤት ስር ሁሉም የተቃዋሚ ኃይሎች ለማሰባሰብ ብዙ የደከምነው፥ ከኤርትራ መንግስትና ህዝብ በሚደረግ ግንኙነት የሚገኝ ፋይዳ ያለው ክንዋኔ ባንድ ወይም በሌላ ድርጅት ብቻ ሳይሆን ቢያንስ ወሳኝ የሆኑ የፖለቲካ ኃይሎች እንዲሳተፉበት በማስፈለጉ ነው። ምክር ቤቱን በሴራ ያፈረሱት በዚህ ሴራቸው ምክንያት ራሳቸውም የፈረሱ ቢሆንም፥ መንገዱ ግን እሱና እሱ ብቻ ነበር፤ ኣሁንም መንገዱ እሱ ነው። ስለሆነም፥ የትጥቅ ትግል ዝግጅት ማድረግ ያለው ጠቀሜታ እንደተጠበቀ ሆኖ፥ ከዚያ በላይ ግን ከኤርትራ መንግስትና ህዝብ የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት ላገራችንና ለህዝባችን የሚያመጣው ዘላቂ ጥቅምና ግኝት ያለው መሆኑን ህዝባችንና የመከላከያ ኃይላችንን በማያሻማ መንገድ በሚያሳምን ጭብጥ ላይ የተመሰረተ መሆን ኣለበት። (ይህንን ጭብጥ በተመለከተ በቀጣይ ፅሁፎቼ በተራ ቁጥር 2 "ከኤርትራ መንግስትና ህዝብ ጋር የሚደረግ ግኑኝነት ለምን?" በሚል ርዕስ ይቀርባል።)[6]

እዚህ ላይ ለማንም ሰው ግልፅ መሆን ያለበት ነገር፥ ሻዕቢያ ከኢትዮጵያዊያኖች ጋር የሚያደርገው ትብብር፥ ሻዕቢያ ራሱን ከመከራና ከውድመት ለማዳን ሲል እንጂ፥ ሻዕቢያ ኢትዮጵያንንና ህዝቧን ለመታደግ ወይም ለፅድቅ ብሎ የሚያደርገው ምንም ዓይነት ችሮታ የሌለ መሆኑን ነው። ከዚህ በተጨማሪ፥ በግልፅና በማያሻማ ቋንቋ መግለፅ የምንፈልገው፥ የኤርትራና የኢትዮጵያ ጉዳይ ተጨባጭ፥ ኣስተማማኝና፥ ዘላቂ የሆነ መፍትሄ እስካላገኘ ድረስ የወያኔ ስርዓት በኢትዮጵያ ቤተመንግስታችን እንዲቆይ ለማድረግ የምንገደድ መሆኑን ነው። የወያነ ስርዓት የዲያብሎስ ስርዓት ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን፥ ኣሁን ባለው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሆኔታና፥ የወያኔን መንግስት ሊተካ የሚችል ኣስተማማኝ ዝግጅት በሌለበት ወቅት፥ የወያነ ስርዓት ለኛ ኣስፈላጊ ዲያብሎስ (necessary evil) ነው። ወያኔን በቦታው ለማቆየት ደግሞ ከሁሉም ስራዎች የቀለለ የቤት ስራ ነው። ከባዱ የቤት ስራ፥ ያንገሽገሸንና ከተሰደድንበት ኣገር ሳይቀር እየተከተለ በሽብርተኝነት የሚከሰንን የወያነ ስርዓት ነቅሎ መጣል ብቻ ነው።

ከሁሉ የከፋው ደግሞ፥ ኣያርገውና፥ ባንድ ወይም በሌላ ምክንያት፥ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ኣዲስ ጦርነት ቢቀሰቀስ፥ ይህን ጊዜ የኣብርሃም ያየህና የተባባሪዎቹ ጎዞ እንደትናንትናው ወደ ኣስመራ፥ ተሰነይ፥ ኣውጋሮና ሓሪና ሳይሆን፥ ወደ ኣዲስ-ኣበባ፥ ዓዲግራትና ሽራሮ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። ይህ ማለት፥ ከሻዕቢያ የሚለገስ የግንቦት ሰባት ጥይት ሰው የሚገድል ከሆነ፥ የመጀመሪያ ሟች ሰው የወያኔ ካድሬ ሳይሆን፥ "የቤቴ መቃጠል ለትኋኔ በጀኝ" የሚባል ፖለቲካ የማይዋጥለት ኣብርሃም ያየህ

[4] http://www.awrambatimes.com/wp-content/uploads/Dialogue_with_G7_Notice.pdf
[5] http://www.ethiopianreview.info/index/?p=546
[6] http://www.awrambatimes.com/wp-content/uploads/Dialogue_with_G7_Notice.pdf

የተባለ ሰው ይሆናል ማለት ነው። እጅግ የሚያሳዝነው ግን፥ ይህ የኔም የመሰሎቼም ፍላጎትና ምርጫ ያልነበረ መሆኑ ነው። ይህንን መጥፎ ምርጫ እንድንመርጥ የሚያስገድዱን፥ ነገር የማይገባቸውና ከነሱ በላይ ለኢትዮጵያ የሚቆረቆር ያለ የማይመስላቸው፥ ነገር ግን ኢትዮጵያ ስትጠፋ እነሱ በሰላም የሚኖሩበት ሌላ ኣገርና ሌላ ዜግነት ያዘጋጁ ጉደኞቹ ትውልደ ኢትዮጵያ ኤሊቶቻችን በተለይ ትውልደ ኣማራ ሊሂቃን ወገኖቻችን ናቸው። (ዝርዝር ምክንያት በቀጣይ ጽሑፎቼ በተለያዩ ርእሶች በስርዓት ይፈተሻል።)

ይህንን ካልኩ ዘንዳ፥ ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መግደል የሚቻልበት መንገድ፥ ወይም መጥፎውን ምርጫ የምንወስድበት በቂ ምክንያት ለመረዳት የሚፈልግ ኃይል ካለ በሚቀጥሉት ተከታታይ ሳምንታት በቅደም ተከተል በሚቀርቡት መጣጥፎቼ ኣማካኝነት የሚሆነውንና የማይሆነውን ሁሉ በጥሞና በመከታተል በሚገባ ለመገንዘብ የሚቻል መሆኑን በቅድሚያ እየጠቆምኩ፤ የኤርትራን ነፃነት ኣስገኘ የተባለለትና <u>ህጋዊ ያልሆነውን ሬፈረንደም</u> ለመቃኘት ባለጉዳዩ "ህዝባዊ ግምባር ሓርነት ኤርትራ (ሻዕቢያ)" ራሱ እ.ኣ.ኣ. በ1980 ዓ. ም. ያቀረበውን የሬፈረንደም ሃሳብ መሰረት በማድረግ እቀጥላለሁ።

**<u>PROPOSALS FOR A REFERENDUM IN ERITREA</u>**<br>
**<u>Made by the</u>**<br>
**<u>Eritrean People's Liberation Front</u>**<br>
**<u>November 1980</u>**

**First, to bring about a peaceful solution for the Eritrean question, hold a referendum in Eritrea in accordance with the just, democratic and correct principle of the right of peoples to self-determination;**

**Second, to implement the first point, set up an international commission acceptable to the Ethiopian Government and the Eritrean Revolution. Its composition would be subject to discussion and could be formed from the United Nations, the Organization for African Unity, the Arab League or the Non-Aligned Movement;**

**Third, reach agreement on a cease-fire and declare it before holding the Referendum and the commission to be set up in accordance with the second point shall monitor and oversee the cease-fire;**

**Forth, from the moment the cease-fire is declared up to the time the referendum is conducted, both the Ethiopian regime and the Eritrean Revolution should have the freedom to carry out political agitation in all zones where there are Eritreans, with all acts of forcible imposition of views prohibited for both sides so the people may express their views with complete freedom;**

**Fifth, the time, places, procedure of registration and method of voting, to be determined and formulated by the commission are to be announced;**

**Sixth, voting shall be based on the following three points: -**

1. **for full independence**
2. **for federal association with Ethiopia**
3. **for regional autonomy**

**Seventh, for any outcome, the Eritrean people shall freely elect their representatives and establish an independent state or administration through a constitutional assembly.**

**Eritrean People's Liberation Front**<br>
**Khartoum**<br>
**November 1980**

**<u>ከህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ</u>**
**<u>በኤርትራ ስለሚካሄድ ሬፈረንደም የቀረበ ሃሳብ</u>**
**<u>ኖቬምበር 1980</u>**

አንደኛ፤ ለኤርትራ ጉዳይ ሰላማዊ መፍትሄ ለማስገኘት፥ ፍትሓዊ፥ ዴሞክራሲያዊና፥ በትክክለኛ የህዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት መርሆ የተመሰረተ ሬፈረንደም ማካሄድ።

ሁለተኛ፤ በአንደኛ ተራ ቁጥር የተመለከተውን በተግባር ለመተርጎም፥ በኢትዮጵያ መንግሥትና በኤርትራ ኣብዮት በኩል ተቀባይነት ያለው ዓለም አቀፋዊ ኮሚሽን ማቋቋም። የኮሚሽኑ ተዋፅኦ በጋራ ውይይት የሚካሄድበት ሆኖ ኮሚሽኑ የተባበሩት መንግሥታት፥ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፥ የዓረብ ሊግ ወይም የገለልተኛ አገሮች እንቅስቃሴ ታክለውበት ሊቋቋም ይችላል።

ሦስተኛ፤ የተኩስ አቁም ስምምነት በማድረግ፥ ይህንኑ ረፈረንደም ከመካሄዱ በፊት ይፋ ማድረግና በሁለተኛው ተራ ቁጥር በተመለከተው መሠረት የሚቋቋመው ኮሚሽን የተኩስ ማቆሙን እንዲከታተልና እንዲቆጣጠር ማድረግ።

አራተኛ፤ የተኩስ አቁም ስምምነት ይፋ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ረፈረንደሙ እስከሚጠናቀቅ ድረስ፥ ህዝቡ ከማንኛውም በኩል ምንም ዓይነት ተጽእኖ ሳይደረግበት በፍፁም ነፃነት ሃሳቡን ለመግለጽ እንዲችል ሆኖ፥ የኢትዮጵያ መንግሥትና የኤርትራ ኣብዮት በማንኛውም ኤርትራዊያን በሚገኙበት ስፍራ ተገኝተው በነፃነት የፖለቲካ ቅስቀሳ ለማድረግ ይፈቀድላቸዋል።

አምስተኛ፤ ጊዜው፥ ቦታው፥ የምዝገባና፥ የድምፅ አሰጣጥ ስነስርዓት በኮሚሽኑ ተወስኖና ተቀነባብሮ ለህዝብ ይፋ ይደረጋል።

ስድስተኛ፤ ለህዝቡ የሚቀርቡለት ምርጫዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፤

1. ሙሉ ነፃነት
2. ከኢትዮጵያ ጋር በፌደረሽን መተሳሰር
3. ራስ ገዝ አስተዳደር

ሰባተኛ፤ በምርጫው ውጤት መሠረት የኤርትራ ህዝብ ያለምንም ተፅእኖ በህገ-መንግስታዊ ጉባኤ ኣማካኝነት የራሱን ተወካዮች በመምረጥ ነፃ ኣገር ወይም ኣስተዳደር ይመሰርታል።

ህዝባዊ ግምባር ሓርነት ኤርትራ
ካርቱም
ኖቬምበር 1980

እንግዲህ፤ ከላይ በግልፅ እንደተመለከተው፥ የጉዳዩ ዋና ባለቤት የሆነው ሻዕቢያ ያቀረበው እንዲህ ያለ ያማረ የሬፈረንደም ሃሳብ እያለ ነበር የወያኔ መሪዎች ገለልተኛ ኣስፈፃሚ ኃይል ባልቆመበትና የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሳተፍበት ሬፈረንደሙ በሻዕቢያ ቁጥጥር ስር ብቻ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ያደረጉት። በሻዕቢያ የቀረበው የሬፈረንደም ሃሳብና በወያኔ መሪዎች ኣስተናጋጅነት የተጠናቀቀው ሬፈረንደም ኣፈፃፀም ሲነፃፀር ልዩነቱ የመሬትና የሰማይ ያህል እንደሚራራቅ ኣንባቢ ይስተዋል የሚል ስጋት የለኝም። ሆኖም፥ ለበለጠ ግንዛቤና ግምገማ ያህል፥ ኣንዳንድ ነጥቦች ለማከል እወዳለሁ።

በሻዕቢያው የሬፈረንደም ሃሳብ በተራ ቁጥር 2 እና 4 የተቀመጠ ኣንድ ጠቃሚ ነጥብ ኣለ። ይኸውም፥ በተ.ቁ.2 "በኢትዮጵያ መንግሥትና <u>በኤርትራ ኣብዮት</u> በኩል ተቀባይነት ያለው ዓለም አቀፋዊ ኮሚሽን ማቋቋም" የሚለውና በተ.ቁ. 4 ደግሞ፥ "የኢትዮጵያ መንግሥትና <u>የኤርትራ ኣብዮት</u> በማንኛውም ኤርትራዊያን በሚገኙበት ስፍራ ተገኝተው በነፃነት የፖለቲካ ቅስቀሳ ለማድረግ ይፈቀድላቸዋል።" የሚለው ነው። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ፥ በሁለቱም ኣንቀፆች ላይ ለኢትዮጵያ የተሰጡት መብቶች በወያነ ስርዓት ያልተፈፀሙ ከመሆናቸው ማሻገር፥ ሻዕቢያ በሁለቱም ኣንቀፆች ላይ ሬፈረንደሙን ያስፈፅማሉ ብሎ የሚጠቅሳቸው ኃይሎች "የኢትዮጵያ መንግስትና <u>የኤርትራ ኣብዮት</u>" በሚል መሆኑ ነው። <u>"የኤርትራ ኣብዮት"</u> የሚለው ሓረግ ሻዕቢያን ብቻ የሚገልፅ ወይም የሚወክል ስም ኣይደለም። ሻዕቢያ የሬፈረንደሙ ኣስፈፃሚዎችን "የኢትዮጵያ መንግስትና <u>ህዝባዊ ግምባር</u>" ብሎ መጥቀስ ተስኖት ወይም ስቶት ኣይደለም። ይሁን እንጂ፥ ጠንቃቃው ሻዕቢያ ይህንን ሓረግ የተጠቀመበትና የመረጠበት ምክንያት፥ ኤርትራ የሻዕቢያ ሞኖፖሊ እንዳልሆነችና ለኤርትራ ጉዳይ የሚታገል ሻዕቢያ ብቻ ባለመሆኑ፥ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ሁሉም የኤርትራ ኃይሎች በሬፈረንደሙ ሂደት መሳተፍ ኣለባቸው የሚል ሃሳብ እንደሚቀርብ የማያጠያይቅ መሆኑን ሻዕቢያ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ነው። ከሻዕቢያ በፊት የተፈጠሩና በኤርትራ ጉዳይ ጥርሳቸውን የነቀሉ ሌሎች ኃይሎች ካልተሳተፉ ሬፈረንደሙን ኣልቀበልም ለማለት ኢትዮጵያ ሙሉ መብት እንዳላትም ሻዕቢያ በሚገባ ያውቀዋልና።

በሻዕቢያው የሬፈረንደም ሃሳብ በተራ ቁጥር 4 ደግሞ ሌላ ወርቅ የሆነ መብት ተፈቅዶልናል። ይኸውም፥ "የተኩስ ኣቁም ስምምነት ይፋ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ሬፈረንደሙ እስከሚጠናቀቅ ድረስ፥ ህዝቡ ከማንኛውም በኩል ምንም ዓይነት ተጽእኖ ሳይደረግበት በፍፁም ነፃነት ሃሳቡን ለመግለጽ እንዲችል ሆኖ፥ <u>የኢትዮጵያ መንግሥትና የኤርትራ ኣብዮት</u> በማንኛውም ኤርትራዊያን በሚገኙበት ስፍራ ተገኝተው በነፃነት የፖለቲካ ቅስቀሳ ለማድረግ ይፈቀድላቸዋል።" የሚል ነው። ይሁን እንጂ፥ "ፅድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በተኮነንኩ" እንዲሉ፥

እንኳንስ ወደ ኤርትራ ሄደን የኤርትራን ህዝብ ልንቀሰቅስ ቀርቶ፥ ሬፈረንደሙ ከመካሄዱና ኤርትራ ገና ነፃ አገር ከመሆኗ በፊት በኤርትራ የነበሩ ኢትዮጵያዊያንና ከኢትዮጵያዊያን ዜጎች የተጋቡና የተዋለዱ የኤርትራ ተወላጆች ወገኖቻችን ጭምር ተጠራርገው እየተዋረዱ ሲባረሩ "ገና ካልለየላት ኤርትራ ዜጎቼ ለምን ይባረራሉ" ብሎ የጠየቀና የተከራከረ የወያነ መሪ አልታየም፤ አልነበረም።

በሻዕቢያው የሬፈረንደም ሃሳብ በተራ ቁጥር 5 ከተካተቱት ቁምነገሮች አንዱ ደግሞ፥ ሬፈረንደሙ የሚካሄድበት ጊዜ በገለተኛው ኮሚሽን የሚወሰን መሆኑን የሚገልፅ ነው። ይሁን እንጂ፥ በወያኔ መሪዎች ቡራኬ የተካሄደው ሬፈረንደም ግን የሚካሄድበትን ጊዜ የወሰነው ሻዕቢያ ብቻውን ነው። የወያነ መሪዎች የተሳተፉት ያንን የሻዕቢያ ውሳኔ በመቀበል ብቻ ነው። ሻዕቢያ የሰጠው ጊዜም ሁለት ዓመታት ነበሩ፤ በነዚያ ዓመታት ደግሞ በኢትዮጵያ በህዝብ የተወከለ ፓርላማም መንግስትም በኢትዮጵያ ምድር አልነበረም።

የሻዕቢያው የሬፈረንደም ሃሳብ በተራ ቁጥር 6 የሰፈረውን ስንመለከት ደግሞ የወያነ መሪዎች ትክክለኛ ማንነት ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። በሻዕቢያው ወርቃዊ የሬፈረንደም ሃሳብ መሰረት፥ ለኤርትራ ህዝብ የሚቀርቡለት ምርጫዎች ሶስት ጠቃሚ ምርጫዎች ነበሩ፤ እነዚሁም፤ 1. ሙሉ ነፃነት፤ 2. ከኢትዮጵያ ጋር በፌደረሽን መተሳሰር፤ 3. ራስ ገዝ አስተዳደር፤ የሚሉ ናቸው። በአንፃሩ፥ የኤርትራ ህዝብ፤ ገና ከብዙ ውዥንብር ሳይወጣ፥ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በመተሳሰር ሊኖረው የሚችል ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ፥ ከኢትዮጵያ ሲለይ የሚገጥመውና ከርሱ አልፎ ለኛም የሚተርፍ ጂኦ-ፖለቲካዊ አደጋዎች፥ ውዘተ. ያለ መሆኑን ሳናማክረው በጥድፊያ በተካሄደው ሬፈረንደም ላይ የቀረቡለት ምርጫዎች፥ እነዚያ ወርቅ የሆኑ ምርጫዎች ሳይሆኑ፤ በምትካቸው "ነፃነት ትፈልጋለህ? ወይስ አትፈልግም? የሚል አስገራሚ ምርጫ ነበር። እንግዲህ፥ የዚህ ዓይነት አስገራሚ ምርጫ የቀረበለት ማንም ሰው፥ ምርጫው ነፃነት ካልሆነ ሌላው የሚቀርለት ምርጫ ባርነት ብቻ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ፥ የኤርትራ ህዝብ ከባርነት ይልቅ ነፃነቱን መምረጡ ትክክል ነበር ብሎ መደምደም ይቻላል ማለት ነው።

ከዚህ የሬፈረንደም ሃሳብ ጋር በተያያዘ ብዙ ነገር ማለት ይቻላል። ከአስራ ሁለት ዓመታት በፊት፥ "የኤርትራ ፋይል ሲከፈት" በሚል 82 ገፅ ያለው መጣጥፌ ላይ እንዳስቀመጥኩት፥ ሬፈረንደሙ ሻዕቢያ ባቀረበው ሃሳብ መሰረት ቢካሄድ ኖሮ የኢትዮጵያን ጥቅም እንዴት ማስከበር ይቻል እንደነበር በዝርዝር ተንትኛለሁ። (ይህንኑ ያልተመለከቱና ለመመልከት የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ፥ የቀሩት መጣጥፎቼ ለህዝብ ከተሰራጩ በኋላ፥ በአውራአምባ ታይምስ በኩል እንዲደርሳቸው ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝ።)

ይህንን ክፍል ከመቋጨቴ በፊት፥ አንድ ነገር ጠቅሸ ልሰናበት። የወያነ ስርዓት በአልጀርስ ስምምነት መሰረት ወደ ሄግ ሄዶ የተከራከረውና፥ ባድመንና ሌላውን መሬት ያስበላው፥ በ18ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የህዝብ ውክልና ባልነበራቸው በአፄ ምኒልክና በፋሺስት ኢጣሊያ መካከል በተደረጉና፥ ጣልያን ኢትዮጵያ ምንም ሳትነካው መላዋ ኢትዮጵያን በመውርሩ ራሱ ያፈረሳቸውን ውሎች መሰረት በማድረግ ነው። የወያነ አመራር፥ ምንም ዓይነት ህዝባዊ ውክልና ሳይኖረውና ሌሎች የኤርትራ ኃይሎች በተገለሉበት ሆኔታ፥ የኤርትራ ሬፈረንደም ሲያስፈፅም ግን ሻዕቢያ ያቀረበው የሬፈረንደም ሃሳብ ዕድሜው አስራ ሁለት ዓመታት ብቻ ያስቆጠረ ነበር።

ቸርነቱ የማያልቀው ኃያሉ ፈጣሪያችን በህይወት አሰንብቶን በቀጣዮቹ መጣጥፎቼ እስክንገናኝ ድረስ ሰላምና ጤና ላንባቢዎቼ ይሁንልኝ! አሜን!